# "ጓደኞችህን ንገረኝና ማንነትህን እነግርሃለሁ"
# ለነበረከት ጓደኛ ለብርሃኑ ነጋ

ከኃይለ ልዑል ግርማ (ዋሽንግተን ዲሲ)

የዶክተር ብርሃኑ ነጋ ከእኔ በላይ አዋቂ ከእኔ በላይ ስለዲሞክራሲ የሚያስበ የለም በሚለው የአራዳው ፍልስፍና ከወያኔ ጋር በፍቅር በኖረባቸው 14 ዓመታት ውስጥ የወያኔን ዘረኛ ፖለቲካ አውቆና ተስማምቶት ስለ ወገኑ ሳያስብና ጉዳይ ሳይሰጠው እንዲያውም የመለስ የኢኮኖሚ አማካሪ ሆኖ፣ ቅዳሜና እሑድ ከጓደኞቹ ከነመለስና በረከት ጋር ቴኒስ እየተጫወተና ማታ ማታ ውስኪ እየተራጨ በወያኔ ሥርዓት ተጠቃሚ ሆኖ ሚሊየነር ለመሆን ከበቃ በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደግሞ የፖለቲካ ታዛዥ ሆኖ በአለቆቹ የሚነገረውን ከመስራት በቀር ከወዳጁ ከብርሃነ መዋ ጋር የተለያዩ የንግድ ተቋማትን ሲያንቀሳቅስና ለራሱ እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይሄ ነው የሚባል ቁም ነገር ሳይሰራ ግርግር ለሌባ ያመቻል ሆነና የተከፈተ የቅንጅት በር ሲያገኝ ሰተት ብሎ ገብቶ ኋላ የመጣ ዐይን አወጣ እንደተባለው በሶስት ወር ጊዜ ዝነኛና የትግል መሪ ለመባል በመብቃቱ ለስንት ዓመታት ሲታገሉ የነበሩ "ፋራዎችን" በልጦ አራዳው ተጠሪም፣ መሪም፣ አዋቂም መስሎ በመታየቱ እና ሕዝብ ደግሞ የወያኔን አገዛዝ መጣል በመፈለጉ ብቻ የእርሱን ማንነትና ተግባር ሳይፈትንና ሳይጠይቅ መሪዬ ብሎ በመቀበሉ የሕዝብን ትግል ማኮላሸት የሚችልበት ደረጃ ደረሰ፡፡

በአጭሩ ዶክተር ብርሃኑ የወያኔና የውጭ መንግሥት ተልዕኮ አስፈጻሚ ነው፡፡ ወደ ትግሉ የገባው ትግሉን ለመቆጣጠር ወይም ለማፍረስ ነው፡፡ ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ከሶስት ሚሊዮን ሕዝብ ተለይቶ ከነመለስ ዜናዊ እና ጓደኞቹ ጋር ሰልፍ ያልወጣ እቤቱ የተቀመጠ ቢኖር አንዱ ብርሃኑ ነጋ ነው፡፡ እቤቴ መሄድ እፈራለሁ ብሎ አና ጎሜዝ ማደሪያ ሼራተን ሆቴሏ ክፍል ውስጥ ያደረው ብርሃኑ ነጋ ነው፡፡ አንድ በሉልኝ ብርሃኑ ነጋ ፈሪ ነው፡፡ ቦቅቧቃ ፈሪ ደግሞ መሪ ሊሆን አይችልም አይገባውም፡፡

ወያኔ ምርጫውን አጭበርብሮ፣ በሰኔ ወር ከ42 በላይ ንጹህ ዜጎች ተገድለው ሰላማዊ ሕዝባዊ አመጽ በተጠራበት ጊዜና ወያኔ ውጭ ነፍስ ግቢ ነፍስ ባለበት ጊዜ የሙት ከተማን አድማ ያከሸፈና ለወያኔ እድሜ መቀጠያ ግሉኮስ ሆኖ ያገለገለው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው፡፡ በዚህም ትልቅ የክህደት ሥራ ሰርቷል፡፡ ስለሆነም ብርሃኑ ነጋ ከሃዲ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ከሃዲ መሪ አይፈልግም፡፡

ስለ ዲሞክራሲና ስለዲሞክራሲያዊ አሰራር ሲያወራ የዲሞክራሲ ፕሮፌሰር እንጂ ከዚያ በታች እውቀት ያለው አይመስልም፡፡ በራሱ በፈጠረው ቀስተ ደመና ውስጥ በአጭር እድሜ ምን ያህል ጸረ ዲሞክራሲ ስራ ሲሰራ እንደነበር አባላቱ በቅርብ ያውቁታል፡፡ ከሶስት ሳምንት በፊት መልምሎ የቅንጅት ምክትል ፕሬዚዳንት ያደረጋት አሻንጉሊቱ ብርቱካን ሚዴቅሳ እና ወደ ለንደን ትግል በቃኝ ብሎ ሲወጣ ኤርፖርት ላይ አንጻርጋቸው ጽጌን በራሱ ሥልጣን የቅንጅት አባልና የላዕላይ ምክር ቤት አባል ያደረገ ብቸኛ ሰው ቢኖር ብርሃኑ ነጋ ነው፡፡ ስለ ዲሞክራሲ እያወራ ጸረ ዲሞክራሲያዊነቱን ያሳየ ሰው ነው፡፡

ፓርላማ በመግባትና ባለመግባት መካከል ያለውን ልዩነት ያላገናዘበና የማያውቀው ብርሃኑ ነጋ ጓደኞቹ ላይ ወያኔ ያደረሰው ወከባ አናዶት ሀሳቤን ለመለወጥ በቃሁ ይላል፡፡ አሜሪካም ከመጣ በኋላ የትግሉ ውልና አቅጣጫ ጠፋብኝ ሲል ደጋግሞ ተናዟል፡፡ መናገር መቻልና ዓላማን ተገንዝቦ በተግባር መተርጎም መቻል የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ እራሱን ሁሉን ነገር አዋቂ ለማድረግ ባለው የመለፍለፍ ችሎታ ሊያደናግር ይሞክራል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ መልሶ ትግሉ አልገባኝም ማሰብ አለብኝ እያለ መቀባጠሩ ምን እንደሚሰራ እንኳን የማያውቅ መሪ ልሁን ይላል፡፡ የሚሄድበትን አቅጣጫ የማያውቅ መጀመሪያ ያንን ሊያውቅ ይገባዋል፡፡ ቅንጅት ግልጽ ያለ ዓላማ እና የትግል ስልት አለው፡፡ ያ ግን ለብርሃኑ ነጋ አይገባውም፡፡ ተልዕኮው ሌላ ነው፡፡ ቅንጣት ያህል የሀገርና የሕዝብ ፍቅር የሌለው ከሃዲ ባንዳ ነውና፡፡

ቃሊቲ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ሴራና ዱለታ መጀመሩ፣ ከሌሎች እስረኞች እየተለየ ይወጣ እንደነበር፣ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ አንድ ሁለት የሃይል ቃል በመናገር ዶክተር ብርሃኑ እንዲህ አለ ተብሎ እንዲነገር በማድረግ ከንቱ ዝና የሚፈልግ፣ እቤቱ እየሄደ ያድር እንደነበር፣ ቆራጣ የኢትዮጵያ ካርታ ሽፋን ያለበት የእኔ እኔ መጽሀፉ ታሪክ፣ ከፍተኛ የጸረ ኃይሉ ሻውል ቡድን ለመፍጠር ሴራ ይጎነጉንና እስረኛውን ይከፋፍል እንደነበር፣ ከውጭ መልዕክተኞቹ ከእነ አንጻርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ ጋር በስልክ ይገናኝ እንደነበር፣ የወያኔን ፈለግ በመከተል በዘር መደራጀትና ለዚሁ የብተና ዓላማ የራሱን ቡድን ያስፋፋ እንደነበርና ከወያኔ የተላለፈበት የዘረኝነት ቫይረስ ይዞት ጸረ አማራ አመለካከት እንደሚያንጸባርቅና በአጠቃላይ የጥፋት መልዕክተኛ እንደነበር ከቃሊቲ ሳይወጣ ያረጋገጠ ሰው ነው፡፡

ከቃሊቲ በወጣ ሳምንት ሳይሞላው ቤተሰቡን ይዞ አሜሪካ ለመቅረት መውጣቱ በራሱ የሚያሳየው ነገር አለ፡፡ ዶክተር ብርሃኑ ሲወጣ ቤተሰቤን ይዤ ዱባይ ቢች ለመዝናናት ወጣሁ አለ፣ አንድ ወር አሜሪካ ተደብቆ ነገሮችን ሁሉ ሲያመቻችና ሲዶልት ሰንበቶ ለሕዝብ የተናገረው ግን እህቴ ቤት ተደብቄ ነበር፡፡ አለ ምን አስደበቀው? አያ ውሸት አያልቅበት፡፡ የሪሰርች ሥራ ለመስራት አሜሪካ እቆያለሁ ሲል ክቡር ከንቲባ የተባለበትን ሃላፊነትስ ምን አደረገው? አንድ ሰው እኮ ፓለቲካ ውስጥ ሲገባና ሃላፊነት ሲወስድ የሕዝብ

አደራና ግዴታ አለበት። አንድም ኃላፊነቱን ውሰዱልኝ ነጻ ሰው ሆኜ እኖራለሁ አሊያም ኃላፊነቴን እወጣለሁ እንጂ የሚያጠናውን የሙያ መስክ እንደማያውቅ ወጣት ተማሪ ግራ የሚጋባበትና ዛሬ አንድ ነገር ነገ ደግሞ ሌላ ነገር ማለቱ ወላዋይነቱን ያሳያል። ሲያሰኘው በጋራ አመራር መሰረት ውሳኔ ወሰንን ይልና ትንሽ ቆይቶ ደግሞ እኔ እንደ ብርሃኑነቴ ነው ይህን የምለው የማደርገው ብሎ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ሲዘባርቅ ደግሞ ይሰማል። ዶክተር አራዳው መናገሩን ብቻ እንጂ አዳማጩ ምን ይላል? ምን ይረዳል? የሚለውን ነገር ፈጽሞ አያጤነውም።

ከቅንጅት ወጥቻለሁ ብሎ ተናግሮ በሳምንቱ ቅንጅት ስብሰባ ውስጥ ተዘፍቆ የማፍረስ ተግባሩን ያካሂዳል። በለንደን የተደረገው ይኼው ነው።  እውነተኛ ብርሃኑ ነጋ ማን እንደሆነ ያሳየበት ነው። ዘረኛ፣ ከሃዲ፣ ሐሰተኛ፣ ቀባጣሪ፣ አወናባጅና ፈሪ መሆኑን ነው ያሳየው። ለዚህም ደግሞ ማንነቱንና ምንነቱን ነው በራሱ አንደበት ገልጾታል። ለመሆኑ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረጣቸው በአማራነታቸው ነው? ምንድነው ታዲያ ብርሃኑ ነጋ የትግሬን አምባገነን አውርደን የአማራ አምባገነን ለመተካት አይደለም ትግላችን የሚለው? ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም አሉ ። የወያኔን የዘር ፖለቲካ አውቆና ተቀብሎ 42 የዩንቨርስቲ ምሁራን ሲባረሩ እነርሱን ተክቶ የገባው ማን ነበር? ለመሆኑ ለቅንጅት እርዳታ ከአሜሪካ የተላከውን ገንዘብ በቀስተደመና ፓርቲ አመራር በኩል ወደ ጉራጌ አገር ይላክ ብሎ የጠየቀውና የወሰነው ማን ነበር? ብርሃኑ ነጋ አይደለምን? ቃሊቲ እያለ የቅንጅት መሪ ተብሎ በዘረኝነት የራሱን ዘመዶችና ጓደኞች በዘር እንዲደራጁና የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ውስጥ በመግባት ያልተጠበቀ የጠባብ ጎሰኝነት የመሰሪ ስራ እንዲሰሩ ያደረገ ማን ነበር? ብርሃኑ ነጋ አይደለምን? የወያኔ ትግሬዎች ወያኔ ሲነካ የትግራይ ሕዝብ ተነካ በማለት የሚጮኹትን ያህል የብርሃኑ ነጋ ሰዎችም ይህን የጠባብነትና የጎሰኝነት ስራቸውን ለመከላከል ብርሃኑ ነጋ ሲጋለጥና ሲነካ የጉራጌ ሕዝብ እንደተነካ የሚጮኹት ያው እርሱ ያሰለጠናቸው ጥቂት የጎሰኝነት በሽታ የያዛቸው እንጂ ሌላው ኢትዮጵያዊ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ አፋር፣ ወላይታ፣ ትግሬ ሳይል አንድነቱንና ኢትዮጵያዊ ባሕሉን ይዞ መከራውን እያየ ነው። ይህ ሕዝብን በጎሳና በዘር መከፋፈል የወያኔና የተከታዮቹ የነብርሃኑ ነጋ ስራ ነው።

ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን መከባበርን በማጥፋት ረገድ የነብርሃኑ ነጋ አጫፋሪዎችን የሚያህል ማንም የለም። ብርሃኑ ነጋም በብልግና አነጋገር አለቃቸው መሆኑን ለንደን ላይ ሰኔ 1 ቀን 2000 ዓ.ም በተናገራቸው የብልግና ቃላቶች ማንነቱን አሳየ እንጂ ኢንጂነር ኃይሉን የጎዳቸው ነገር የለም። በተግባር ሲታይ ግን የሞራል ዝቅተኛነቱን ያሳየው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው። በዋሽንግተን ዲሲ ሬስቶራንቶች እስከ ሌሊቱ ስምንትና ዘጠኝ ሰዓት ድረስ አልኮል ጠጥቶ ሲንገዳገድ ያየነውና እራሱን ያዋረደው እርሱ እንጂ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል አይደሉም። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ቶሮንቶ ከተማ በሚገኝ የነጮች ጭፈራ ቤት ከጓደኛውና ከሁለት ሴቶች ጋር ሲጠጣና ሲጨፍር ያመሸው ብርሃኑ ነጋ እንጂ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል አይደሉም። ከቃሊቲ ሆኖ መጽሐፍ ጻፍኩኝ ካለ ጀምሮ እስከ ዛሬ ሲዋሽና ሲቀላምድ የነበረው ብርሃኑ ነጋ ነው። ከነጮች ጋር በመመሳጠር የቅንጅትን ትግል አቅጣጫ ለማስቀየር የዶለተው ብርሃኑ ነጋ ነው። ኸረ ስንቱ ተቆጥሮ የብርሃኑ ነጋ ጉድ። ታዲያ ወዴት የአብዬን ለእምዬ ዶክተር ብርሃኑ?. ጸረ አማራነትህን ራስህው አጋለጥክ። ዘረኛ መሆንክህን በገዛ አንደበትህ መሰከርክ። የነማን ጓደኛ ሆንክና ድሮስ።

ግንቦት 7 ንቅናቄ የሚለው ነገር ሌላ የማወናበጃና የማጭበርበሪያ መንገድ ነው። ዋናው ዓላማ በውጭ ያለውን ተቃዋሚ ለመከፋፈል፣ ገንዘቡን ለመዝረፍና የዋሆችን በማነሁለል ትግሉን ለማዳከም ነው። አሊያማ ብርሃኑ ነጋ ወደ አገር ቤት መመለስ አለበት። ያንን ደግሞ አያደርገውም ምክንያቱም ገና ከቃሊቲ ሳይወጣ ጀምሮ ውጭ ለመቅረት የወሰነው ስለሆነ ነው። ለመሆኑ ውጭ ያሉ ደጋፊዎቹ ብርሃኑ ነጋ ዋሽንግተን ዲሲ ሆኖ ሁለገብ ትግል እንዴት ሊያካሂድ ይችላል ብለው ለምን አይጠይቁም? እነ OLF ሌሎችም በመሳሪያ እንታገላለን የሚሉት ሽብርተኛ ተብለው ተፈርጀው ብርሃኑ ነጋ ነጻ የሆነበት ምክንያት እንዴት ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። በገንዘብ ተገዝተው የሚንቀሳቀሱት ለሆዳቸው ነው ሌሎች ግን ተታለው የሚጓዙትን መንገዳቸውን እንዲያርሙ በተደጋጋሚ አሳውቀናል።
ብርሃኑ ነጋ ከራሱም ቡድን አልፎ የኢሕአፓ አንጃ የሆነውን የመርሻን ቡድን የትግል አጋሩ አደርጎ ለመለስ በረከት ይዞ ለመግባት ያደረገው ሙከራም መዘንጋት የለበትም። ሁለቱም ክፍሎች የሚጠብቁት የ2010 ምርጫ ጊዜን ስለሆነ ሕዝብ መሰሪ አካሄዳቸውን ሊከታተለው ይገባል። ፍጥምጥማቸው አልቋል ሰርጋቸውን አዲስ አበባ በምርጫው ሰሞን መሆኑንም አውቀናል። የባንዳ እና የአንጃ ጋብቻ ቢጠቅም ለነመለስ ብቻ እንጂ ለሕዝብ አይደለም። ቢሸፋፍኑት ካባ ቢደርቡበት ባንዳም ባንዳ አንጃም አንጃ ነው የአንድ ሳንቲም ገጽታዎች።

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ከወያኔው መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ሌላ እንደልባቸው በነጻነት በሕዝብ መካከል መንቀሳቀስ ከማይችሉት ሰዎች መካከል አንዱ ልደቱ አያሌው ሲሆን ሌላው ብርሃኑ ነጋ ነው። ምክንያቱም የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል የከዱ ባንዳዎች በመሆናቸው ነው ሕዝብ መካከል ብቻቸውን በነጻነት መንቀሳቀስ የማይችሉት። ብርሃኑ ነጋም ይህንን ያውቃል።

ኢንጂነር ኃይሉ ግን በሕዝባቸው መሀል ከሕዝባቸው ጋር ለሕዝባቸው ትግል ቆመዋል በተግባርም እያሳዩ ናቸው። ፤ አገር ቤት ያለው ሕዝብም ሆነ እኛ የምንከተለው ሀቀኛና ጀግና መሪ እርሳቸውን ብቻ ነው።